

# ፨49-2፨

# ተጠንቀቁ!
## ራስ ወዳድነት ትምክህተኛ ያደርጋል

(ካለፈው የቀጠለ)

በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው ግልጽ የሆነ ስህተት በሚደርግም ራሱን የሚከላከልባቸው ምክንያቶችን ይፈጥራል። ለምሳሌ፥

"የእኔ ችግግሬ ንግግሬ ሁሉ ፊት ለፊት በመሆኑ ነው፤

"ግልጽ በመሆኔ ነው፤

"እንደ ሰው የሚሰማኝን ባለመደበቄ ነው"

"ስሜቴ በቀላሉ ስለሚጎዳ ነው…"

"ይህን አጠፋሁ ብዬ የማስታወሰው ነገር የለኝም" ይላል።

ሀ. 5. ስለ ራሱ ብዙ ያወራል

በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው የሰራውን ያደረገውን ያገኘውን አተልቆና አጋኖ አሳምሮና ቀባብቶ ማውራት ይወዳል። ምን ያህሉ እርሱ ጸልዮላቸው እንደተፈወሱ እርሱ ሰብኮላቸው እንደዳኑ የሚይወራበትን መንገድ ይፈልጋ። ዲ. ኤል. ሙዲ የተባለው ታላቅ የእግዚአብሔር አገልጋይ "አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ እንደሄደ ማወቅ የሚቻለው ስለ ራሱ ጥሩነትና ስለሠራቸው ሥራዎች ብዙ መናገር ሲጀምር ነው" አለ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላቸዋል፤ "እኔ ሀብታም ነኝ፤ ብዙ ሀብት አለኝ፤ የሚጎድለኝ ምንም የለም ትላለህ፤ ነገር ግን ጎስቋላ፣ ምስኪን ድሃ፣ ዕውር፣ የተራቆትህም መሆንህን አታውቅም" (ራዕይ 3፥17)።

ሀ.6. ከሌሎች ተሽሎ መታየት ይፈልጋል

በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው ከሌሎች ተሽሎ ለመታየት ብቻ ምንም ዓይነት ዋጋ ይከፍላል። የህጻን ልጁን ወተት መግዣ ለራሱ ማጌጫ ልብስ ቢገዛበት ትንሽም ህሊናውን አይቆረቁረውም። ከሌሎች በልጠ ለመታየት ከአቅሙ በላይ ይኖራል። በዚህ ምክንያት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውጥረት ሲደርስበት፣ የተጭበረበረ፣ የተምታታና ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነ ኑሮ መኖር ይጀምራል። ለመስረቅ፣ ለመዋሸት፣ የራሱ ባልሆነ ገንዘብ ለመጠቀም የተጋለጠ ይሆናል። ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው የእግዚአብሔር ቅቃል መልዕክት አለው፤ "ሀብታም መስሎ በችግር ከሚኖር ሰው ይልቅ ተራ ሰው መስሎ እየሠራ ኑሮውን የሚያሸንፍ ይሻላል" ይለዋል (ምሳሌ 12፥9)። አንድ ጸሐፊ "ከውሸት ሁሉ አሳፋሪው በምላሳችን የምንዋሸው ውሸት ሳይሆን፥ በኑሮአችን የምንዋሸው ውሸት ነው" አለ።

ለ. በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው፥ ከሰው ጋር እንደተጋጨ ይኖራል

እግዚአብሔር ሰው ብቻውን እንዲኖር አልፈጠረውም። ከሌሎች ሰዎች ጋር በህብረት እንዲኖር ይፈልጋል። ብዙ ጊዜ ደግሞ የሰው ችግሩ ሌሎች ሰዎች ናቸው። በአካባቢው ሰዎች ባይኖሩ የሚያጋጥመው ችግር የተወሰነ ይሆን ነበር። ሰው ከሌላው ጋር የሚኖረው ግንኙነት ጥሩ ወይንም መጥፎ እንዲሆን የሚያደርገው፥ ስለ ራሱ የሚኖረው ግምትና አስተያየት ነው። ራሱን ብቻ በጣም የሚወድ፥

ለ.1. ሁልጊዜ ከሌሎች ጋር ይጋጫል

"ራሱን ብቻ የሚወድ" (egoist) ራሱን ከሰዎች ሁሉ በላይ አድርጎ ስለሚያቀርብ፥ ሥፍራውን የሚወስድበት ስለሚመስለው ብዙ ጊዜ በግጭትና በፍርሃት ውስጥ ይኖራል። "ራስ ወዳድ የሆኑ ሰዎች ከሌሎች ጋር ተስማምተው መኖር አይሆንላቸውም፤ ሌሎች ሰዎች ትክክል አለመሆኑን አውቀው የሚያምኑበትን እርሱ ይቃወማል" ይላል ምሳሌ 11፥1-2። ሰውን አያምንም፣ ለሰላምታቸው እንኳን የተሳሳተ ትርጉም ይሰጠዋል። ይህን

ዓይነት ችግር የሚኖራቸው ያልተማሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንዲያውም ከፍተኛ ትምህርት በቀሰሙት ላይ ይበልጥ ሲያይል ይታያል። ተምሬአለሁ የሚለው ከሌላው ከተማረው መማር አይፈልግም። መጋቢው ከሌላ መጋቢ መማር ደስ አይለውም። "ራሱን ብቻ የሚወድ" ሁልጊዜ "ማሸነፍ አለብኝ" ይላል። ሌላው ቀርቶ ጊዜ ለማሳለፍ ከወዳጁ ጋር በሚጫወተው ጨዋታ እንኳን ካላሸነፈ ከወዳጁ ጋር ግጭት ይፈጥራል።

**ለ. 2. ተወዳድረው ማሸነፍ የማይችሉ ከመሰላቸው፥ ፈራጅ ይሆናሉ**

"እኔነቴ ይደፈራል" ብለው የሚፈሩ አንዳንድ "ራስ ወዳዶች (egoist) ራሳቸውን በፈቃዳቸው ከውድድሩ ያስወጣሉ። የሚወጡትም "እሸነፍ ይሆናል" ብለው ስለሚፈሩ ነው። ይሄ መንፈስ "ራስን ከፍ አድርጎ ከማየት" ነጻ ያደርጋቸዋል ማለት አይደለም። ራሳቸውን ከሌሎች ከፍ አድርገው የሚያሳዩበት መንገድ በሌሎች ላይ መፍረድ ነው። "ዳኛ ሆነን እንፍረድባችሁ የምንላቸው ሰዎች በእነርሱ ላይ ፈራጅ መሆናችንን ስለማይወዱት በቀላሉ እንጋጫለን።

**ለ. 3. መብለጥ ካልቻለ፥ ሌሎችን ማጥፋት ይፈልጋል**

"ራሱን ብቻ የሚወድ" በመንገዱ የቆሙ የመሰሉትን ሁሉ ከማጥቃት ወደ ኋላ አይልም። ጥላቻው የሚታየው በውስጡ በሚይዘው ቂም ወይንም ቅሬታ ነው። የሰውን ሕይወት ከሚያበላሹት ስሜቶች መካከል "ከበደለኛነትና ከቁጣ" ቀጥሎ ያለው "ቂም" ወይንም ቅሬታ ነው። ቂመኛ ሰው ፊት ለፊትም ሆነ በተዘዋዋሪ፥ በቃላትም ሆነ በተግባር ቂም የያዘበትን ሰው የማጥቃት ዝንባሌ አለው። ትንሽ የምትመስለው "ቅሬታ" በሰው ሕይወት ተጠራቅማ ስታድግ ሌላውን ብቻ ስይሆን ቂመኛውንም ከጉዳት ላይ ይጥላል።

**6. "ራስ ወዳድነት" (egoism) ጎጂ ነው**

በዓለም ውስጥ ይህ ችግር የሌለበት ሥፍራ የለም። ችግሩ ትንሽ፣ ትልቅ፣ ወንድ፣ ሴት፣ የተማረ፣ ያለተማረ እያለ ሰውን አይመርጥም። ዘመኑ ያመጣው ችግር ብቻ ሳይሆን ጥንትም የነበረ ነው። ቃየል ወንድሙን አቤልን ገደለው። የገደለውም አቤል በድሎት ሳይሆን ከእርሱ ይልቅ እግዚአብሔር በአቤልና በመስዋዕቱ ደስ ስላለው ብቻ ነው (ዘፍጥረት 4፥4-7)። ሰዎች በራሳቸው ፍቅር በመስከራቸው ምክንያት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በዓለም ዙሪያ አልቀዋል። የፈረንሳዩ ንጉሥ ቻርለስ ዘጠነኛው "ለእኔ በመስገድ ፈንታ ለጳጳሱ ሰግዳችኋል" በማለት ብቻ በአንድ ቀን ውስጥ 150 ሺ ሰዎች ህጻናት ሳይቀሩ በሰይፍ እንዳሳረዳቸው ታሪክ ይናገራል። በራሳቸው ፍቅር በሰከሩ ሰዎች ምክንያት የብዙዎች ቤት፣ ትዳር ፈርሷል። ልጆች ያለወላጆቻቸው እንዲያድጉ ሆነዋል። የሚዋደዱ ጓደኞሞች ተለያይተዋል። ይሄ መንፈስ ብዙ ቤተ ክርስትያንን አፍርሷል፣ ብዙ መዕመናንን እርስ በርሳቸው ከፋፍሏል፣ ብዙ መንፍሳዊ አገልግሎቶችን አዘግቷል።

በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው ራሱም ቢሆን ደስተኛ አይደለም። ሁኔታዎች ተመቻችተው ካልቀረቡለት ስዎች እርሱ እንደሚፈልገው ካልሆኑለት የአዕምሮ ጭንቀት ይይዘዋል። "እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን! የእኔ ፈቃድ ብቻ ይፈጸም!" ስለሚል ከሌላው ሰው ጋር ተስማምቶ በሰላም መኖር አይሆንለትም። ሕይወቱ ሁልጊዜ የጦርነት፣ የግጭት ሕይወት ነው። የታወቀው ግሪካዊ አልሲቢያደስ ዓለምን ዞሮ ያየ ዕድለኛ ሰው ቢሆንም፥ ፍጹም ደስታ የሸሸው ሰው ነበር። አንድ ቀን የታወቀውን ግሪካዊ ፈላስፋ ሶቅራጥስን "ለምንድነው አልሲቢያደስ ደስተኛ መሆን የማይችለው?" ሲሉ ጠየቁት። ሶቅራጥስም ሲመልስ "የኤልሲቢያደስ ችግር በሄደበት ሥፍራ ሁሉ ራሱን ይዞ ስለሚሄድ ነው" ሲል መለሰላቸው። ይህን ሲል ችግሩ የሚመጣው ከውጪ ሳይሆን ከራሱ ውስጥ የሚመነጭ መሆኑን ሲገልጽላቸው ነው። ሰው የችግሩ ምንጭ ራሱ መሆኑን መገንዘብ ሲችል፥ ከራሱ ለመሸሽ ከመሞከር ይልቅ ከራሱ ጋር መታረቅ የሚችልበትን መንገድ መፈለግ ያስፈልገዋል።

## ከራስ ፍቅር ለመላቀቅ መፍትሄው ምንድነው?

**የምሥራቃውያን ፍልስፍና የራሱ መልስ አለው**

ሀ. 1. የምሥራቃዊያን ፍልስፍና የሰው ችግሩ "ሰው ራሱ" እንደሆነ ይናገራሉ። ሰው በሕይወቱ እስካለ ድረስ ከችግር ነጻ መሆን አይችልም። ከመከራ (ከችግር) ሰው ነጻ ለመሆን ቢፈልግ የግል ስሜቱንና ፍላጎቱን መግደል አለበት፤ በሕይወት እንዲቆይ የሚያደርገው ያ በውስጡ ያለው የግል ፍላጎቱ ነው። ስለዚህ ያንን ሕይወቱን የሚያሽከረክረውን "ፍላጎት" መግደል ሲችል ያኔ ራሱን ከመኖር ወደ አለመኖር ይለውጣል፤ ከመከራም ነጻ ይሆናል ይላሉ።

ሀ. 2. ሌላው የምሥራቃውያን ፍልስፍና የዘመኑ "ሰው በራሱ ብቃት አለው" የሚሉ (Humanist) ሰው ራሱን "አምላክ ነኝ" ብሎ እንዲቀበልና እንዲያምን ያስተምራሉ። ሰው ራሱን እንደ "አምላክ" ለመቀበል በብዙ ፍለጋና ትግል ውስጥ ያልፋል። የሚያሳዝነው ሰው ራሱን እንደ "አምላክ" ከመቀበል ደረጃ ሳይደርስ በዓለም የተመደበለትን

ዘመን ጨርሶ የሚያልፍ መሆኑ ነው። ይሄ ፍልስፍና የፈለቀበትና ሥር የሰደደበት አገር ሕንድ ሲሆን፥ እስከ አሁን "እኔ አምላክ ነኝ፣ መለኮታዊ ነኝ" ብሎ ራሱን ከመቀበል ደረጃ የደርሰ የለም። ሰው ተፈጣሪ ስለሆነ ምንጊዜም ቢሆን "አምላክ" መሆን አይችልም። ዘማሪው "ከመላዕክት ትንሽ አሳንሰህ ፈጠርከው" ይለዋል። ይሄ "ከመላዕክት ትንሽ አንሶ የተፈጠረው ሰው፥ እግዚአብሔር መጀመሪያ ሲያበጀው "አምላክ" እንዲሆን አይደለም። ስለሆነም ሰው ተፈጥሮውን ለቆ ራሱን "አምላክ" ለማድረግ ሲሞክር ከራሱና ከእግዚአብሔር ጋር ይጋጫል። በልቡ ዙፋን ላይ ሊቀመጥ የሚገባውን ጌታ ከህይወቱ ያስወጣል።

**ለ. የሥነ አዕምሮ ጠቢባን የራሳቸ መልስ አላቸው**

ለ. 1. "ሰው ከችግር ራሱን ነጻ ለማድረግ፥ ራሱን ማስወገድ ብቻ ነው" የሚለውን የምሥራቃውያን ፍልስፍና የማይቀበሉ የዘመኑ የሥነ አዕምሮ ጠቢባን የራሳቸው መልስ አላቸው። ይኸውም አንደኛ "ራስህን እወቅ" የሚለው ሃሳብ ነው። ችግሩ ግን ሰው ራሱን ማወቅ የሚችለው እንዴት ነው? ራሱን ማወቅ የሚችለው ራሱን ከራሱ ጋር ወይንም ራሱን ከሌሎች ሰዎች ገር በማነጻጸር ነው? በዚህ ቁሳቁሳዊ ዓለም ውስጥ ከኖረ ስለራሱ የሚኖረው ዕውቀት በምድራዊ አቋም ላይ የተመሠረተ ብቻ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በጥሶ ሲጥል፥ ሕይወቱ ትርጉምና ዓላማ የሌለው ይሆናል።

ለ.2. የዘመኑ የሥነ አዕምሮ ጠቢባን ሰው ላለበት ችግር መፍትሄ ይሆናል ብለው የሰጡት ሁለተኛው መልስ "ራስህን ተቀበል" የሚለውን ሀሳብ ነው። ጥያቄው ግን ሰው በውስጡ ትልቅ ግጭት፣ ትልቅ ቅራኔ፣ የበደለኛነት፣ የዝቅተኛነት ስሜት የሞላበት ሆኖ እንዴት ራሱን እንዳለ ሙሉ በሙሉ መቀበል ይችላል? ሊቀበለው የማይችለውን "ተቀበል" ማለት "የሕሊናህን ክስ አታዳምጥ" ብሎ መምከር ይሆናል። የዘመኑ የሥነ አዕምሮ ጠቢባን "ራስህን ተቀበል" ብለው ሰውን ሲመክሩ "የሕሊናህን ክስ አታዳምጥ" ማለታቸው ብቻ ሳይሆን፥ "እግዚአብሔርንና ሕጉን ክደህ ኑር" ማለታቸው ይሆናል። ይሄም ችግሩን ከማቃለሉ ይልቅ በውስጡ የበለጠ ግጭትና ቅራኔ እንዲፈጠር ያደርጋል።

**ሐ. ክርስቶስ የራሱ መልስ አለው**

ሐ. 1. በግለሰብም ደርጃ ሆነ በማህበር የሰው ትልቁ ችግር የሚመነጨው ከውጪ በሚመጣ ችግር ሳይሆን ከውስጥ "ከእርሱነቱ" በሚመጣው ነው። መፍትሄ ለማግኘት በመጀመሪያ ያንን "እርሱነቱን" በግድ ማስተካከል አለበት። እርሱነቱ መሰቀል ሲገባው ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ እንደሆነ፥ ለፈውሱ ሲል ትክክለኛ ቦታውን በግድ መያዝ አለበት። በሰው ሕይወት የሚታየው አብዛኛው ችግር ከግል ፍላጎቱ የመነጨ መሆኑን ለማመን አያስቸግረንም። ለምሳሌ ሰዎች ራሳቸውን መቆጣጠር እስከሚያቅታቸው ድረስ የሚናደዱት ለምንድነው? አብዛኛውን ጊዜ ሌላው የእነርሱ የሆነውን ወይንም "እነርሱነታቸውን" የነካባቸው ሲመስላቸው ነው። ሰዎች ለምን ይዋሻሉ? የተሻለ ጥቅም የሚያገኙ ሲመስላቸው ነው። ሰዎች ከቅድስና ውጪ ለምን ይኖራሉ? በዚያ ውስጥ የተሻለ (የበለጠ) ደስታ የሚያገኙ ስለሚመስላቸው ብቻ ነው። ሰዎች ለምን ምቀኛና ቀናተኛ ይሆናሉ? ሌላው ሰው ከእነርሱ እንዲቀድም ወይንም እንዲበልጥ ስለማይፈልጉ ነው።

ሐ. 2. ሰው ሥር ነቀል ለውጥ ያስፈልገዋል። ይሄም መሆን የሚችለው ለሙሉ ለውጥ ልቡን የከፈተና ያዘጋጀ እንደሆነ ነው። ቀጥሎም ራሱን ከልቡ ዙፋን ላይ አውርዶ "ጌታ ሆይ ይኸውልህ እንካ! በልቤ ዙፋን ላይ ተቀምጥ" ብሎ ሙሉ በሙሉ ማስረከብ ወይንም መስጠት ሲጀምር ነው። ሰው የልቡን ዙፋን ለሚገባው ንጉሥ ለጌታ ለኢየሱስ ሲለቅ ምን ይሆናል? ከመኖር ወደ አለመኖር ይለወጣል ማለት ይሆን? ዓላማቢስ፣ ዋጋ የሌለው ለራሱም ሆነ ለሌላው ጥቅም የማይሰጥ ፍሬ ቢስ ይሆናል ማለት ይሆን? ምንጊዜም ቢሆን ሰው "እርሱነቱን" ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አይችልም። ዛሬ "እርሱነቱን" በበር ቢያስወጣው፥ ነገር በመስኮት ይገባል። ጴጥሮስ ኢየሱስን አንድ ጊዜ "እኛ ሁሉን ትተን ተከትለንሃል፤ ታዲያ ምን እናገኛለን?" ሲል ጠየቀው። ጴጥሮስ "ሁሉን ትተናል" ይበል እንጂ በእርግጥ ሁሉንም አልተወም ነበር፤ ቢተው ኖሮ "ምን እናንገኛለን?" ብሎ ባልጠየቀም ነበር።

ሐ.3. ሰው ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ሲሰጥ "ራስ ወዳድ" የሆነውን ሕይወቱን ያንጻል። ራሳችንን መስጠት ስንጀምር፥ እግዚአብሔር ፈቃደኛነታችንን ስለሚያገኝ፥ ወደ ውስጥ ዘለቅ ብሎ የችግራችን ሁሉ ምክንያት የሆነውን "ራስ ወዳድነታችንን" ከውስጣችን ማጥፋት ይጀምራል። "እሺ" ስንለው የእግዚአብሔር ሕግ ወደ ውስጣችን ዘልቆ በመግባት ከዚህ በፊት ያልታየን እንዲታየን ያደርጋል። ያም የእግዚአብሔር ሕግ "ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ያጣታል…" የሚለው ለዚህ ነው። ራሱን "መካከለኛ" ወይንም "ዋና" የሚያደርግ ሁሉ "እርሱነቱና" ፈቃዱ የተዛባ ይሆናል። ራሱን ብቻ የሚወድ ሰው መሠረቱ የተናጋበት ሰው ነው። ይሄም በመሆኑ ራሱን ይጠላል፤ በሌሎችም ሰዎች የተጠላ ይሆናል። የእግዚአብሔር ሕግ ከላይ በጠትቀስነው ዓይነት ብቻ አያበቃም። "…ሕይወቱን ስለ እኔ ሲል የሚያጣ ግን ያገኛታል" ይላል። ይህም ማለት ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስናስገዛ ራሳችንን በማጣት ፈንታ መልሰን እናገኘዋለን ማለቱ ነው። ራሳችንን

በእግዚአብሔር እግር ሥር ስንጥል ነጻ ሆነን በዓለም መመላለስ እንችላለን። ለእርሱ ስንገነበስ፣ በሌላው ሁሉ ፊት ቀጥ ብለን እንቆማለን። ራሳችንን ለጌታ "እንካ" ብለን ማስረከብ ስንችል፥ የእኛን ፈቃድ በእርሱ ፈቃድ መለወጣችን ነው። ያኔ ማድረግ የማንችለውን እንድንችል፥ መሆን የማንችለውን እንድንሆን እንሆናለን፤ ለውጣችንም እኛን ብቻ ሳይሆን ከውጪ ሆነው ለሚያዩንም አስደናቂ ይሆናል።

ሐ. 4. ራስን ሙሉ በሙሉ መስጠት "ሞት" የለበትም ማለት ይሆን? አዎን አለበት! ቢሆንም የተለየ ሞት ነው። እውነትነት ለሌለው (artificial) ሕይወት ማስመሰል ለሞላበት ሕይውት ኃጢአት ላለበት ዓለም፥ "እኔ ብቻ" ለሚለው የሕይወት ፍልስፍና የሞትን እንሆናለን። ጳውሎስ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" ሲል ከላይ ለጠቀስናንቸው ኃጢአቶች "ሞቻለሁ" ማለቱ ነው እንጂ በሥጋ "ከመኖር ወደ አለመኖር ተለውጫለሁ" ማለቱ አለነበረም። ከክርስቶስ ጋር በሕይወት መኖር ማለት ትንሳኤ ባገኘው "እኛነታችን" ክርስቶስ በውስጣችን ሆኖ የምንኖረው ሕይወት ነው።

ሐ. 5. ራስን መስጠት የሚቻለው በፍቅር ብቻ ነው፤ ያም ከፍተኛ ፍቅር ነው። ይህን ዓይነቱንም ስጦታ መስጠት የምንችለው ለታላቁ አምላክ ብቻ ነው። ራስን ለትዕቢት፣ ለሥጋ አምሮት፣ ለገንዘብ፣ ለመራራነትና ለጥላቻ እንዲሁም ለፍርሃት አሳልፎ መስጠት መጥፎ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሞኝነትም ነው። ራሳችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ "እኛነታችን" ፈጽሞ ጠፍቶ በሕግና በሥነ ሥርዐት የምንታሰርበት፥ "ይህን፣ ያን አታድርግ" የምንባልበት ሕይወት ሳይሆን ለመኖር ለማፍቀር በሙሉ ነጻነት የምንመላለስበት ሕይወት ነው። እንግዲህ የተሟላ ሕይወት አሸናፊ ሕይወት ለመኖር ከፈለግን "በራሳችን ፍቅር" ከመያዝ ነጻ እንሁን።

..........................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**